ጊዜ ያልፋል ፥ ጊዜ ይተካል ፤ አሁንም ሆነ ባለፈው ጊዜ ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያለንን መሠረታዊ ግንኙነት ሊቃውንቶቻችንም ሕዝቡም ያውቁታል ። ከግብፃውያን ወንድሞቻችን ጋር የሚያስተሳስረን የሃይማኖት ጉዳይ ነው ። ሃይማኖት ደግሞ እኔ የያዝኩት ብቻ ነው ማለት አይገባም ። ለማንም ቢሆን ከሃይማኖቱ ክርሱ ከራሱ የበለጠ ፈጣሪውን የሚያውቅለት የለም። ከዚህም የተነሣ በእግዚአብሔር መንግሥት ሥልጣን ዳኝነት ሰው ሊገባ አይችልም ። የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ራሷን ለማስቻል ጥረት ከተጀመረበት ከብዙ ዓመታት በፊት አንስቶ ጉዳዩ እያደገ እንዲሄድና ከዚህም ደረጃ እንዲደርስ ለማድረግ የነበረው ድካም ያለፈበትን መንገድ ስናስብ ክባድነቱ የሚዘነጋ አይደለም ። አሁን እግዚአብሔር የሚሠራውን ሥራ በፈቀደ ጊዜ ስለሚፈጸም ኢትዮጵያ አገራችን ፥ ነፃ ሕዝባችንና መንግሥታችን ራሷን የቻለች ቤተ ክርስቲያን እንዲኖራቸውና በዓለምም እንዲታወቁ ካደረገ ብለን ስለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት ዕድለኞነት የተናገርነውን ቃል በዚህ ቀን ልናስታውሰው ይገባል ። ምክንያቱም ቸርነቱ ስለቀጠለልንና እንዳለፈው ዛሬም አሳባችንን ስለፈጸመልን ነው ።

በዚህ አረማመድ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያዊ ሊቀጳጳስ እንዲሾምላት ከተደረገ በኋላ ሁለተኛውን ማዕርግ ለማግኘት የሚያስፈልገው ኢትዮጵያዊ ፓትሪያርክነት ስለሆነ ከዚህ ተያይዞ የተገኘው የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ መሾም አሁን ደግሞ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፍጹም የሆነ የራስ መቻል ማዕርግ ማግኘት ደስታችንን እጥፍ አድርጎታል ። ለታሪካችንም ምስክር ነው ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፓትርያርክ ሆነው በተሾሙ ጊዜ ፥ እኛ ራሳችን ካይሮ ተገኝተን ስለነበረ ደስታውን ተካፍለን ነበር ።

ነገር ግን የሰው ልጅ በዚህ ዓለም ነዋሪነቱ ዘለዓለማዊ ባለመሆኑ ተግባራቸውን ፈጽመው ከኛ በመለየታቸው የሚሰማን ኃዘን ጥልቅ ነው ። ዘወትር የማይሰለቸው እግዚአብሔር ለነፍሳቸው ዕረፍት ይስጥ እንላለን ።

በዚያን ጊዜ ለተገኘው ውጤት በአፍሪካ መካከል የክርስቲያን ደሴት ሆና የኖረችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚገባትን ትልቅነት ና ክብር እንድታገኝ በዘመናችን ደክመንበታል ። ድካማችንን ባርኮ ይህንን ፍሬ እንድታፈራ ላደረገልንና ኢትዮጵያዊ ፓትሪያርክ በማግኘቷ ለኢትዮጵያ የተገባትን ይህን ቀን ለማየት ላበቃን ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና እናቀርባለን ብለን እንደተናገርነው ሁሉ ፥ ዛሬም በዚህ ቀን ፥ የምናቀርብለት ምስጋና ለርሱ ሥራ ዋጋ አይሆንም እንጂ ከፍ ያለነው ።

የእግዚአብሔር ቸርነት ዘለዓለም የማይወሰን እንደመሆኑ ምስጋናውም በሰማይ ባሉ መላእክትና በምድርም ባሉ ሠራዊት ዘንድ ሲነገር ቢኖር የማያልቅ ስለሆነ ዛሬም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፓትሪያርክ ዘኢትዮጵያ ሆነው በመሾማቸው ክብር ምስጋና ለርሱ ይሁን ።

ከብዙ ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ መምህራን በፊት የጳጳስነት መዐርግ ፥ በኋላም የሊቀጳጳስነት መዐርግ በማግኘታቸውና ከዚያም ቀጥሎ ለተደረገላቸው ሁሉ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን ።

ለዚህ ለተባለው ሁሉ የደከምነው ድካም በእግዚአብሔር ዘንድ የተባረከ ሆኖ ራስን በራስ የማስቻል ጠንካራ አቋቋም ስለተመሠረተ ወደፊት በዚህ ረገድ አስቸጋሪ ነገር ይኖራል ብለን አናስብም ።

ዘመናችንን የመንፈሳዊ ክብር ዕድገትና የብሔራዊ ስሜት መምሪያ አድርጎ በየ ጊዜው የደከምንበት በጊዜው ሲፈጸምና ባፈጻጸሙም ለሕዝባችን በሥጋውም በነፍሱም የሚጠቀምበት መንገድ እየተቃና በመሔዱ ደስ ሊለን ይገባል ።—

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የቤተ ክርስቲያናችንን ዕድገት በአለፈውም ሆነ በአሁኑ ዘመናችን እንዲፈጸም ዕድል ስለአገኙ በዚህም ዕድል ቤተክርስቲያናችን በሙሉ መብት ላይ ተቋቁማ ስትገኝ ደስታው ለተሿሚው ለተሾላሚው ብቻ ሳይሆን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ።

አባቶቻችን ነገሥታትና የኢትዮጵያ ምእመናን ሁሉ ዐይነ ሕሊናቸውን ወደሰማይ አቅንተው የሚጠብቁት ዕድል በአሁኑ ትውልድ ጊዜ ወርዶ በእጃቸው ሲጨበጥ ያዩ ዐይኖች ብፁዓን አይደሉምን ፤ ስለዚህ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፥ያስጨበጧትን የመብትና የብርሃን ፋና እየደመቀና እየጐላ እንዲሄድ የማድረጉ ኃላፊነት የብፁዕነትዎ ነው ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ። ለኢትዮጵያ የሁለተኛው ጊዜ ለሆነው ለዚህ ከፍተኛ ፓትረያርክነት ማዕርግ በቅተው ከባድ አደራ ያለበትን የፓትረያርክነት ተግባርዎን ሲጀምሩ ሥራዎን ለማከናወን እግዚአብሔር ይርዳዎ ።

ይህን የዛሬውን ታሪካዊ ቀን ለማክበር የደስታችን ተካፋይ ለመሆን በተሰበሰቡት ሁሉ ደስታው የመላው ኢትዮጵያውያን መሆኑን ተመልክተነዋል ። እግዚአብሔር ደስታችንን የአፍ ሳይሆን የልባዊ አድርጎ ይባርከልን ።—